# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ሐምሌ 16 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**የወያኔ ቱባ ባለስልጣን ሀገር ጥሎ ኮበለለ፤**

**የክልል ባለስልጣናት ስራቸውን በገዛ ፍቃዳቸው እየለቀቁ ነው ተባለ፤**

**የወያኔ ካድሬ የሆኑት የምክር ቤት አባሎች ወያኔን አወገዙ፤**

**በሀገሪቱ አስጊ የጎርፍ አደጋ ሊከሰት እንደሚችል ተጠቆመ**

የወያኔ ቡድን በሚሰራው ሸፍጥ የተነሳ በገዛ ካድሬዎቹ ውስጡ እየተቦረቦረ መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የወጣው ጥቆማ አጋለጠ፡፡በተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊነት ቦታ ላይ ሲሰሩ የነበሩ የወያኔ ባለስልጣናት በሚደረግባቸው ግፊት እና ጫና በገዛ ፍቃዳቸው ስራቸውን እየለቀቁ ወደ ውጭ ሀገር እየኮበለሉ በመሆኑ ወያኔ ለከፍተኛ ኪሳራ እየተዳረገ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ሰሞኑን የተለያዩ የስልጣን እርከን ቦታዎች ላይ የተቀመጡ የወያኔ አፈድፋጅ ባለስልጣናት ስርዓቱን እየከዱ ወደ ተለያዩ ሀገራት እየኮበለሉ ጥገኝነት እየጠየቁ መሆኑን ተከትሎ በወያኔ የተለያዩ መስሪያ ቤት ውስጥ ጥብቅ ግምገማ እየተደረገ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

የአማራ እና የኦሮሚያ ክልል ካድሬዎች አኩርፈው ባለበት በዚህ ግዜ ባለስልጣናት እና የወያኔ አድር ባዮች ስራ በገዛ ፈቃዳቸው እየለቀቁ ከመሆኑም በተጨማሪ ስርዓቱን እየከዱ ወደ ውጭ ሀገር እየኮበለሉ በመሆኑ የተደናገጡት የወያኔ መሪዎች እና የደህንነት ከፍተኛ ባለስልጣናት ማንኛውም ባለስልጣን ከሀገር ሲወጣ ፍቃድ ማግኘቱን የሚያሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው ክፍል መያዝ አለበት በሚል ከቦሌ አየር ማረፊያ እየመለስዋቸው መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በኦሮሚያና በአማራ ክልል የተለያዩ ዞኖች ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ዳኞች በሚደርስባቸው ወከባና እንግልት ብሎም ማስፈራሪያ የተነሳ ስራቸውን በገዛ ፍቃዳቸው እየለቀቁ ወደ መሀል ሀገር

ከመምጣታቸውም በተጨማሪ አንዳንዶቹ ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ከሀገር እየኮበለሉ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

ሰሞኑንም የወያኔ ቀንደኛ ካድሬ የሆነው ለገሰ አለሙ የተባለው ግለሰብ ለስራ ተብሎ ወደ አሜሪካ ተልኮ የሄደ ቢሆንም በዚያው ስርዓቱን ከድቶ መቅረቱን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

በፍትህ ሚኒስትር በምክትል ሚኒስትር ማዕረግ የህግ ጥናት ማርቀቅ እና ማስረጽ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆነው ይሄው ግለሰብ ከፍትህ ሚኒስትሩ ብርሀን ኃይሉ ጋር ከአሜሪካ ከፍተኛ የህግ ኤክስፐርቶች ጋር ተገናኝተው ለቀናት ውይይት ሲያደርጉ የሰነበቱ ቢሆንም ከውይይቱ በሁዋላ በዚያው ሀገር መቅረቱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አብራርተዋል።

ከፍትሕ ሚኒስትሩ የብአዴኑ ከፍተኛ ሰው ከሆነው ብርሀን ኃይሉ ጋር ልምድ ለመቅሰም ተልኮ የነበረው ግለሰብ በወያኔ መሪዎች ጫና እየተደረገበኝ ስራዬን በነጻነት ለመስራት አልቻልኩም በሚል በዚያው በሀገረ አሜሪካ የቀረ ሲሆን ሰሞኑን ጥገኝነት መጠየቁንም ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ተናግረዋል።

በአንድ ወር ውስጥ ብቻ በኦሮሚያና በአማራ ክልል ውስጥ የሚሰሩ የፍትህ አካላት ቁጥራቸው የበዙት በገዛ ፍቃዳቸው እየለቀቁ ......ገሚሱ ጠበቃ እየሆኑ......ሌሎች ደግሞ ባገኙት ስራ ላይ ሲሰማሩ..... ብዙዎቹ ግን ስርዓቱን በመክዳት ወደ ውጭ ሀገር እየኮበለሉ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በሁሉም መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች እና በክልሎች ደረጃ ግምገማ እንዲደረግ ታዝዞ ሰራተኛውን የማስፈራራት ዘመቻ መጀመሩም ታውቆዋል።

በአሁኑ ሰዓት በፌዴራል ፖሊስ ፣በማረሚያ ቤት ፖሊሶች እና በአዲስ አበባ ፖሊሶች እንዲሁም በአቃቤ ህጎች ላይ በየቦታው በመከፋፈል ጥብቅ ግምገማ እያደረጉ ሲሆን በሚደረገው ግምገማ ላይ የመክዳት አዝማሚያ አሳይተዋል የተባሉት ላይ ሀሰተኛ የሙስና ክስ እየተመሰረተ የዋስ መብታቸው ሳይጠበቅ ለእስር እየተዳረጉ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮች በተለይ የማረሚያ ቤት ነባር መኮንኖች በዚህ መንገድ ተጠልፈው ብዙዎቹ እስር ቤት እየታጎሩ መሆኑን የምንጮቹ ጥቆማ አብራርቶዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥም በተደረገ ግምገማ ከ120 ባለስልጣናት በላይ ልባችሁ ሸፍቶዋል ከእኛ ጋር አይደለም ተብለው የሀሰተኛ የሙስና ክስ ተዘጋጅቶባቸው ወደ ዘብጥያ ሊወርዱ በዝግጅት ላይ ሲሆኑ ከነዚህ መሀከል ከ20 የማያንሱት በተለያዩ ዘዴዎች ሀገር ጥለው መኮብለላቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል።

በመሬት አስተዳደር.....በፍትህ ቢሮ....በንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮና በሌሎችም መስሪያ ቤት ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ የወያኔ ባለስልጣናት ከግዜ ወደ ግዜ በጥቂት የወያኔ ቡድን መሪዎች የሰለቸና የመነቸከ ትዕዛዝ በመበሳጨት ስራቸውን እየለቀቁ ቢሆንም በቅርቡ ተደረገ በተባለ ግምገማ ከያሉበት ተለቅመው ወደ ዘብጥያ ለማውረድ የሙስና ክስ እየተዘጋጀባቸው መሆኑን ምንጮቹ አብራርተዋል።

ይሄው የወያኔ ቡድን አጨብጫቢ የሆነው ግለሰብ መኮብለሉን ተከትሎ ለወያኔ መሪዎች ትልቅ የራስ ምታት እንደፈጠረባቸውና እርስ በርስ እየተተራመሱ እንደሆነ የጠቆሙት ምንጮቹ ከእንግዲህ በህጋዊ መንገድ ወደ ውጭ ለመውጣት የሚፈልግ ባለስልጣን ከሚፈለገው የደህንነት አካል ፍቃድ ሳያገኝ መውጣት እንደማይቻልም ምንጮቹ አብራርተዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሁለት እውቅ አርቲስቶች የወያኔን ስርዓት ጠልተው ከሀገር በመኮብለል ጥገኝነት መጠየቃቸው ታወቀ:: አምስቱ እርጎዬዎች ተብለው ከሚታወቁት አንዱዋ የሆነችው ድምጻዊት እየሩሳሌም ዱባለ እና ባለቤትዋ ድምፃዊ አበበ ፍቃዱ የተባሉት ባልና ሚስቶች ወደ ካናዳ አቅንተው ጥገኝነት መጠየቃቸው ታውቆዋል::

ወያኔ በሚያዘጋጃቸው የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኛ አይደላችሁም እየተባሉ ብዙ ግዜ በደህንነት ባለስልጣናት እንግልት እና ወከባ ሲደረግባቸው እንደነበረ ያጋለጡት የአርቲስቶቹ ቤተሰቦች የምሽት ክለብ ከፍተው በግላቸው ለመስራት ቢሞክሩም ደህንነቶች እየገቡ ሰካራም በመምሰል እየበጠበጡና እያወኩ በማስቸገራቸው ያለ ስራ ለዓመታት እንደቆዩና አሁን ግን አጋጣሚውን ሲያገኙ ወደ ካናዳ አቅንተው ጥገኝነት ለመጠየቅ እንደቻሉም ከቤተሰቦቻቸው ገለፃ ለመረዳት ተችሎዋል::

ከዚህ ቀደም ከአርቲስቶች እና ከተመልካች ጋር አጋጭተዋት የነበረችው የሀገር ፍቅር ቲያትር ዋና ስራ አስኪያጅ አርቲስት መንበረ ታደሰ በሚደርስባት ጫና የተነሳ ስራዋን በገዛ ፍድዋ ከመልቀቅዋ በተጨማሪ ስርዓቱን ከድታ አሜሪካ መግባትዋ ይታወቃል::

አርቲስት መንበረ ታደሰ በአርቲስቶች መሀከል ከፍተኛ ክፍተት እንዲፈጠር ብሎም ሁሉም ለወያኔ እንዲያጎበድድ የተሰጣትን ተልዕኮ በአግባቡ በመወጣትዋ የአዲስ አበባ ምክር ቤት አባል እንድትሆን የተደረገችና ከተራ ሰራተኛነት ተነስታ የነባሩና የአንጋፋው ቲያትር ቤት የሀገር ፍቅር ዋና ስራ አስኪያጅ እንድትሆን ተደርጎ ለዓመታት የወያኔ ዋና ሎሌ ሆና ስታገለግል ብትቆይም በሁዋላ ግን ፍቅራቸው ባለመዝለቁ ስራዋን በገዛ ፍቃድዋ በመልቀቅ ስርዓቱን ከድታ ዛሬ በምድረ አሜሪካ ኑሮዋን መስርታ እንደምትገኝ ታውቆዋል::

በተያያዘ ዜና እጅ አውጡ ሲሉዋቸው የሚሰቅሉ...አውርዱ ሲሉዋቸው የሚያወርዱት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተባሉት የወያኔ ካድሬዎችም ከነበረከት የሚደርስባቸውን የአፈና አገዛዝ በመቃወም የወያኔን ባለስልጣኖች ሲያወግዙና ሲያስጠነቅቁ እንደሰነበቱ ተሰማ::

እነዚሁ የምክር ቤት አባል ተብዬ የወያኔ ካድሬዎች ሰሞኑን የሁለት ቀን የክረምት ውይይት ተብሎ በሂልተን ሆቲል በተረደገ ስብሰባ ላይ እኛ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎች የመረጠንን ህዝብ ብሶት በተለያዩ አጋጣሚዎች ይፋ ብናደርግም በራዲዮና ቲሌቪዥን እንዳይሰራጭ እየታፈነ ይልቁንም የስራ አስፈጻሚውን ሚና እና ድርሻ እያጎላችሁ እኛን ደግሞ እያኮሰሳችሁ መገኘቱ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያሳፍር ወደፊትም ተጠያቂ የሚያደርጋችሁ ነው ሲሉ እነሽመልስ ከማልን ሲያስጠነቅቁ መዋላቸው ታውቆዋል::

ከሐምሌ 7 ቀን እስከ ሐምሌ 8 ቀን 2003 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፌዴራልና ከክልል ሚዲያና ኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት ኃላፊዎች ጋር በተደረገ የምክክር መድረክ ላይ

የቋሚ ኮሚቴውንና ዋናውን መደበኛ ስብሰባ የምናደርገውን ክርክር ለህዝብ ይፋ የማታደርጉና ተገቢውን ሽፋን የማትሰጡ ናችሁ ካሉ በሁዋላ በተለይ በመንግስት ባለስልጣናት ላይ የምንሰጠውን አስተያየት እየቆረጣችሁና እያፈናችሁ በምክር ቤት አባላት እንደተወደሰ እያደረገችሁ የምታቀርቡት አካሔድ ወደፊት አብረን ለመዝለቅ የሚያስቸግር ከመሆኑም በላይ እኛ የምክር ቤት አባሎች የሁሉም መንግስታዊ ተቋዋም የበላይ ሆነን ሳለ እያኮሰሳችሁንና እያወረዳችሁን የበታች እያደረጋችሁ ምንም ስራ እንዳልሰራን ማቅረባችሁ በታሪክና በትውልድ ከመጠየቅ አልፎ በወንጀል ጭምር እንደምትጠየቁበት ልትገነዘቡ ይገባል በማለት አፅንኦት ሰጥተው ሲከራከሩ እንደሰነበቱ ከተሰብሳቢዎቹ ተደምጦዋል::

የፓርላማ ወንበሩን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው የወያኔ ቡድን የገዛ ካድሬዎቹ ተማርረውበት ባለሰልጣኖቻችን ለማወገዝ መድፈራቸው ከምን የተነሳ መሆኑን ማወቅ ባይቻልም በወያኔ ችግር መኖሩን ያመላክታል ሲሉ ታዛቢዎች አስተያየት ይሰጣሉ:: የወያኔው መሪን መለስ ዜናዊን ጨምሮ ሚኒስትሮችን በድፍረት እያወገዙ ያሉት የወያኔ ካድሬዎች ቡድኑ መበስበሱንና መቆጣጠር አለመቻሉን ብሎም ከእንግዲህ ምን ይመጣል በሚል እየተናገሩ ከመሆኑም በላይ ወንጀለኞች ናችሁ በማለት ማውገዝ መጀመራቸው ምሁራኖችንና ህዝቡን እያነጋገረ የመጣ ጉዳይ ሆኖዋል::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ የወያኔ ቁንጮ ባለስልጣናት እና ካድሬዎቹ ሆድና ጀርባ የመሆናቸው ዋና ቁልፍ ጉዳይ ስርዓቱ መዳከሙን ያመላከተ ነው ያሉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራኖች ወያኔ ውስጡ መበስበሱን ቁልጭ አድርጎ ያሳየም ነው ብለዋል::

በሌላ ዜና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የጎርፍ አደጋ ሊከሰት እንደሚችል የሜትሮሎጂ ባለሙያዎች ከወዲሁ እየገለፁ ባለበት ወቅት የወያኔ ቡድን አንዳችም ቅድመ ዝግጅት አለማድረጉ ተጋለጠ::

በአሁኑ ወቅት መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሊዘንብ ስለሚችል አስቀድሞ ቅድመ ዝግጅት ሊደረግ ይገባል በማለት የሜትሮሎጂ ባለሙያዎች ቢወተውቱም የወያኔ ቡድን ግን ከህዝቡ ይልቅ ለሱዳን አቤይ ግዛት ትኩረት በመስጠት ሰምቶ እንዳልሰማ በመሆን እያምታታ መሆኑ ታወቀ::

ባለሙያዎቹ እንዳስታወቁት በአሁኑ ሰዓት በምእራብና በሰሜን ምዕራባዊ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም የመሀከለኛውን ጨምሮ በአማራ፣በጋምቤላ እና በአፋር ክልሎች ከባድ የጎርፍ አደጋ ሊከሰት እንደሚችል ስጋታቸውን እየገለፁ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ የምግብ እጥረት ሊከሰት ይችላል ተብሎ በባለሙያ ከተጠቆሙት ስፍራዎች ዜጎችን የማስነሳት ስራ መሰራት ሲገባው በቸልታ እንደ ተራ ነገር በመቁጠር ወያኔ እያድበሰበሰ እንደሚገኝም ባሙያዎቹ በብስጭት ይገለጻሉ::

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ከ5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ለከፍተኛ ርሀብ ተገልጠው በሚኙበት በዚህ ግዜ እንደገና የጎርፍ አደጋው ሊከሰት እንደሚችል በመገለፁ የተረጂ ወገኖች ቁጥር ወደ 11 ሚሊዮን ሊያሸቅብ እንደሚችልም እነዚሁ ባለሙያዎች ከወዲሁ ስጋታቸውን ደጋግመው እየገለፁ ይገኛል::

የወያኔ ቡድን በሀገሪቱ የተከሰተውን የርሀብ አደጋ ምንም እንዳልተፈጠረ አድርጎ ደብቆ የቆየ ቢሆንም ችግሩ ሰፍቶና ገዝፎ ከወጣ በሁዋላ ሳይወድ በግድ ይፋ የሆነ ሲሆን አሁንም የጎርፉ አደጋ ሊያስከትል የሚችለውን ለመቀነስ ዘዴ ከመፈለግ ይልቅ በልበ ድፍንነት ምንም ችግር አይፈጠርም በሚል ዝምታን መምረጡ በእጅጉ የሚያሰዝን እና የሚያሳፍር መሆኑንም ባለሙያዎች ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት በድሬዳዋ ድንገተኛ የጎርፍ አደጋ ተከስቶ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በጎርፉ ተወሰደው መሞታቸውና በሺህዎች የሚቆጠሩት ደግሞ ቤት ንብረታቸውን አጥተው ለተፈናቃይነት መዳረጋቸው የሚታወስ ሲሆን የአሁኑ አስቀድሞ መከላከል ሲቻል ወያኔ ዝምታን በመምረጡ አደጋው የከፋ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ ስጋት ማሳደሩ ታውቆዋል።